DeKalb County
School District

ሴፕቴምበር 12/2016

ውድ የ DeKalb County የት/ቤት አውራጃ ቤተሰቦች

የሁሉም ተማሪዎች እና ሰራተኞች ጤና እና ደህንነት ቅድሚያ ትኩር የምንሰጠው ነው፣ ትኩረት መስጠታችንን ለወደፊትም እንቀጥላለን።

ይህን ካልን፣ የ DeKalb County የት/ቤት አውራጃ በእያንዳንዱ 150 ት/ቤቶቻችን፣ ማዕከሎቻችን እና አመቻቾቻችን ባላቸው የመጠጥ ውሀ ውስጥ ሊድ መኖሩን በንቃት እየመረመረ ነው።

በቅርቡ የተፈጠሩ ሁኔታዎች የሀገርን ትኩረት ወደ ውሀ ጥራት ጉዳዮች ስቧል። እባክዎ **በማንኛውም ት/ቤት ወይም ህንጻ ውስጥ የውሀ ጥራት ችግሮች ማስረጃ በፍጹም እንደሌለን ይረዱ።** አሁንም፣ ውሀችን ለመጠጥ ደህንነቱ የተጠበቀ እንደሆነ ተማሪዎች፣ ሰራተኞች እና ማህበረሰቡ እንዲያውቁ እንፈልጋለን።

ምርመራው የሚጀምረው ሴፕቴምበር 20ኛ ነው። ከ DeKalb County የጤና ቦርድ እና DeKalb County መንግስት ጋር በመተባበር በሚከተሉት ላይ ናሙና እንወስዳለን፦

- ሁሉንም ዋና ለህንጻዎች ውሀ የሚያስተላልፉ ቱቦዎች
- ሁሉንም ኩሽናዎች
- ሁሉንም የውሀ ምንጮች
- የሽንት ቤት እጅ መታጠቢያዎች
- የበረዶ ማሽኖች
- በመምህራን ክበቦች የሚገኙትን የውሀ ምንጮች
- የስፖርት ሜዳዎች

ከአውራጃው ቀደምት የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች እንጀምር እና ለት/ቤቶች የተዘጋጀ የአካባቢ ጥበቃ ኤጀንሲ (EPA) መመሪያዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ እያንዳንዱን ቦታ ሁለቴ እንመረምራለን። **ማንኛውም ናሙና በ EPA ደረጃዎች የሊድ መኖርን ከጠቆመ ውሀ ከዛ መጠቀም ወዲያውኑ እናቆማለን፤ በመቀጠልም ችግሩን እናስተካክላለን ወይም እናስወግዳለን።** ካስፈለገ ችግሩ እስኪስተካከል ድረስ የታሸገ ውሀ እናቀርባለን።

የምርመራው ውጤቶች በደብዳቤ ይደርስዎታል እንዲሁም በአውራጃው ድህረ-ገጽ **www.dekalbschoolsga.org/lead-testing**ላይ ይገለጻል። የውሀ ጥራት እና የሊድ ምርመራን በተመለከተ ለአዳዲስ ነገሮች እና ለተጨማሪ መረጃ እባክዎ ድህረ-ገጻችንን ቶሎ ቶሎ ይጎብኙ። ተጨማሪ ጥያቄዎች ለ**DCSD_Communications@dekalbschoolsga.org** መላክ ይችላሉ።

የተማሪዎቻችንን እና ሰራተኞቻችንን ጤና እና ደህንነት ስለምንጠብቅ ሂደቶቹን በሙሉ ልናሳውቅዎት ዝግጁ ነን።

ከሰላምታጋር

ዶ/ር R. Stephen Green
ዋና ተቆጣጣሪ
የ DeKalb County የት/ቤት አውራጃ

S. Elizabeth Ford, M.D.
የአውራጃ የጤና ዳይሬክተር
የ DeKalb County የት/ቤት አውራጃ

Lee May
ጊዜያዊ ዋና ስራ አስፈጻሚ
የ DeKalb County የት/ቤት አውራጃ